<u>መጥኔ!</u>

ከከበቡሽ አየናቸው
**02/0109**

አዬ የወያኔ ብያኔ!
ታምራትን ወደ ምናኔ፣
ብርቱካንን ወደ ኩነኔ::
ታምራት ምናኔን ከትግል ቢመርጥም፣
ከተጠያቂነት ፍፁም አያመልጥም::
ለምናኔ ምርጫ ለስግደት የበቃው፣
እርሱ ያደራጀው ለሌሎች የሠራው፣
የቃሊቲ ሲዖል ስላስመረረው ነው::
ለብርቱዋ ፍጥረት ብርቱካን ሚዴቅሳ፣
ግርማዋ ሚያስፈራ እንስቲቱ አንበሳ፣
አየደለም እንግዳ የቃሊቲ አበሳ::
ለዚች ታላቅ ጀግና የጨቅላ ልጅ እናት፣
የወያኔው ሥርዐት ፍርደ-ገምድል መንግሥት፣
ልዩነት የለውም ከቃሊቲ እሥር ቤት::
ሕግ የበላይ ሆኖ ፍትህ ካልተከበረ፣
ያገር እሥር ቤት ነው ለኖረም ላልኖረ::
ፍትህ ካለተከበረ ሕግ የበላይ ሆኖ፣
ዜጋ ካልኖረበት በሕግ ተማምኖ፣
ያገር ወህኒ ቤት ነው የጠፋበት መቅኖ::
እነርሱ ያሉትን ካልሆነ በስተቀር፣
ዕውነትን መናገር ዕውነትን መመሥከር፣
በማይቻልበት የቀጣፎች አገር፤
የወያኔ መንጋ ኢሕአዴግ ጥርቅም፣
በሚጨፍርበት በዚያ ክፍለ-ዓለም፣
ከወህኒ የሚሻል ምንም ኑሮ የለም::
ከርቼሌ ወረዱ፣ ታሠሩ አልታሠሩ፣
ከርቼሌ ከሆነ ጠቅላላ ሀገሩ፣
ለዳኛ ብርቱካን ግልፅ ነው ሚስጥሩ::
እንደስማዕቲቱ ለአለ ብርቱ ጀግና፣
ታሠሩ አልታሠሩ ምን ዋስታና አለና?!
የብርቱካን የትግል ይዘት፣
ፍትህ እንዲሰፍን በአንድነት፣
ሠላም እንዲነግሥ በነፃነት፣
አገር እንድትለማ፣ እንድትፋፋ፣
ረሃብ ድንቁርና እንዲጠፋ፣
አብሮነት እንዲጠነክር፣
ኢትዮጵያዊነት እንዲከበር፣
ይህ ነበር በዕውነቱ የእርሷ ፍላጎቷ፣
የትግል ዕመነቷ ራዕይ ምኞቷ::
ኢትዮጵያዊ በዜግነቱ፣
እኩል ይጠበቅ መብቱ፣
ቅጥፈት ይወገድ፣ ዕውነት ትንገሥ፣
አታላይነት የትም አያደርስ፤
ስላለች ብቻ ሕጉን ጠቅሳ፣
የደነገጉትን ተንተርሳ፣
ለምን ያሳዩዋታል አበሳ?!
ረሀብን ለማጥፋት ቆርጣ ስትታገል፣
እንደምን በረሃብ እንደዚህ ትቃጠል?!
ያቺን ብርቱ ፍጥረት ማን ይታደጋታል?
የረሀቡን አድማ ብርቱካን ስትመርጥ፣

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

መኖርን ጠልታ ነው ግፉን ልታጋልጥ፡፡
እንደጉልበት ቆጥራ የረሃቡን አድማ፣
ብርቱካን ትታመም ተጎሳቁላ ደክማ?!
ነግ በእኔ ነውና ጆሮ ያለህ ስማ፡፡

እርሷም ጉልበት የላት እኛም ጉልበት የለን፤
እባክህ ፈጣሪ ታደጋት፤ ታደገን!!!
አንድ ሆኖ ሲያጠቃን ጥርቅም ወያኔ፣
እስከመቼ ለቅሶ እስከመቼ ወይኔ?
እባክህ አንድ ሁን ይሰማህ ወገኔ፡፡
መጠላለፍ ይብቃ፤ መታገል በሾርኔ፤
ከዚህ የበለጠ ምን አለ ኩነኔ?
አረ ተው ተጋለጥን፣ መጥኔ! መጥኔ! መጥኔ!

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com